Australian Government
Department of Home Affairs

# ነጻ የትርጉም አገልግሎት

## በኮቪድ-19 ምክንያት በአገልግሎቶች የተደረጉ ለውጦች

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው እና ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው ሰዎች በኮቪድ-19 ክስተት ወቅት ጥራት ያለው የትርጉም አገልግሎት መጠቀም እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

ሰዎች በሚገኙበት ጊዜ የአስተርጓሚ አገልግሎት መጠቀም አለባቸው፡፡

ስለ **ኮቪድ-19 እና ምልክቶቹ** ለመማር ድህረገጹን ይከፈቱ፡፡

## ነጻ የትርጉም አገልግሎት ምንድ ነው?

ነጻ የትርጉም አገልግሎት እርስዎ መጠቀም የሚችሉት፡-

- አወስትራሊያዊ ከሆኑ
- መዲኬር ካርድ ካለዎት፤ እንዲሁም
- ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ ካለዎት ነው፡፡

## ነጻ የትርጉም አገልግሎት እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የሚከተሉት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እርስዎን ወክለው ነጻ የትርጉም አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡-

- የግል የሕክምና ባለሞያዎች
- ፋርማሲስቶች
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
- የሪል እስቴት ድርጅቶች
- የአከባቢ መንግስት ባለስልጣናት ለምሳሌ የአከባቢው ማዛጋጃ ቤቶች
- የሠራተኛ ማህበራት፤ እንዲሁም
- የፓርላማ አባላት፡፡

ስለእነዚህ የአገልገሎት ሰጪ ድርጅቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት **እዚህ**.ይመልከቱ፡፡

በራስዎ ቋንቋ መረጃ እና ምክር ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሱት አገልግሎት ሰጭዎች ከስልክ አስተርጓሚ ጋር በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሊያገናኝዎ ይችላሉ ፡፡

# አስተርጓሚዎች

የተርጓሚዎች እና አስተርጓሚዎች ብሔራዊ እውቅና ሰጪ ባለስልጣን (NAATI) እውቅና የሰጣቸው አስተርጓሚዎች ብቻ እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ አስተርጓሚዎች በባለሙያ የሥነምግባር ደንብ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ይህ ደንብ የተዘረዘሩትን እንዲከተሉ ይጠይቃቸዋል፡-

- መረጃን በትክክልና በሐቀኝነት መተርጎም
- ምስጢራዊነትን መጠበቅ
- አድልዎ የሌለበትና ተግባራዊ መሆን፤ እንዲሁም
- በማንኛውም ጊዜ ሁሉንም እንደ ሙያዊ አካሄድ መተግበር፡፡

የነጻ አስተርጓሚ አገልግሎት ፖሊሲ ከፍተኛ እውቅና የተሰጠው አስተርጓሚ መጠቀም ነው። በዚህ ምክንያት የተወሰኑ አስተርጓሚዎችን መጠየቅ አይበረታታም ፡፡

# ነጻ የትርጉም አገልግሎት ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ይሰጣል?

- አስቸኳይ የስልክ አስተርጓሚ አገልግሎት። ይህ አገልግሎት ላልታቀዱ ትርጉሞች በጣም ጠቃሚ ነው፤ የሚከተሉትም አቅርቦቶች አሉት፡-
    - በ 160 በሆኑ ቋንቋዎች የሚሰሩ ከ 3,000 በላይ አስተርጓሚዎች ይገኙበታል
    - በቀን ለ 24 ሰዓታት ፣ በሳምንት ለ 7 ቀናት የአስተርጓሚ አገልግሎት ይሰጣል
    - ከደውሉ በኋላ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከአስተርጓሚ ጋር ያገናኛል፡፡
- ቅድሚያ የታቀደ የስልክ አስተርጓሚ አገልግሎት፡፡
    - የህ ለታቀደ የትርጉም አገልግሎት ፣ ወይም ብዙም ያልተለመደ ቋንቋ መጠየቅ ከፈለጉ ጠቃሚ ነው፡፡